የሚሽነሪዎች ወጥመድ

በሀገራችን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቁጥር በከፍተኛ ሁናቴ እያሻቀበ እንደሆነ ይነገራል። እምነታቸውን ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ከሚቀይሩት ውስጥ ደግሞ የሙስሊሞች ቁጥር የማይናቀውን ድርሻ ያነሳል። የሙስሊሞች ጉዳይ ፀሀፊዎቹ ኢስሀቅ እሸቱ ፣ አክመል ነጋሽ እና ሰለሞን ከበደ የሚሲዮናውያን አጥማቂዎችን መረብ ፈትሸው የቁጥራቸውን መጨመር እንቆቅልሽና የመዘናጋታችንን ከፍታ በተከታዩ ፊቸራቸው ያስነብቡናል።

‹‹አብደላ ቀልቤሳ እባላለሁ። በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ውስጥ ተቀጥሬ ለረጅም ዓመታት አገልግያለሁ። በስራዬም ታታሪ ነኝ። አንድ ቀን ቢሮዬ ውስጥ ተቀምጬ የእለቱን ሥራዎች በማከናወን ላይ እያለሁ አንድ ክርስቲያን ወጣት በርካታ መጽሐፍ ቅዱሶችን ይዞ ወደ መ/ቤታችን ገባ። በየቢሮዎችም ውስጥ እየገባ ለሁሉም ሠራተኞች በነፍስ ወከፍ አንድ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ በገፀ በረከትነት አበረከተልን። በመሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ሰዎች ልጁ በፈጸመው ተግባር ተበሳጭተው ለዱላ ተጋበዙ። በዚህ መሀል ነበር እኔ ከመሀል ገብቼ ልጁን ከድብደባ ያዳንኩት። ‹መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖችን ወደ እስልምና ለማምጣት ልንጠቀምበት ስለምንችል መቀበላችን አይከፋም› ብዬ ለባልደረቦቼ ሀሳቤን አቀረብኩላቸው። ብዙዎቹ ሀሳቤን በቀና ተመልክተው ‹‹ገፀ-በረከቱን›› ተቀበሉ።

ይህ የገለጽኩት ትዕይንት ከተፈጸመ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ለሥራ ጉዳይ ወደ ክልል ከተማ ተጓዝኩ። በደረስኩበት ከተማ ሁለት ክርስቲያን ወጣቶች መጥተው ስለ አምላክ (God) ፍቅርና ከኢጋንንት የመፈወሳቸውን ምስክርነት ሰጡኝ። ወዲያው ‹እኔም እኮ ባምን ኖሮ ከኢጋንንት ተፈውሼ ከሰይጣን ቀንበር ነፃ እወጣ ነበር› ብዬ አሰብኩ። በዚህች ቅጽበት የሆነ ስሜት የሠራ አካሌን እንደ ኤሌክትሪክ ሲነዝረኝ ተሰማኝ። ሁኔታው ለኔ ድንገቴ ነበር። ጊዜ ሳላጠፋ ‹መካነ ኢየሱስ› ቤተክርስቲያንን ለመጎብኘት ሄድኩ። በቦታው ያገኘሁትንም ፖስተር ፀሎት ያደርግልኝ ዘንድ ጠየቅኩት። መልካም ፍቃዱ ሆነና ፀሎቱን ጀመረልኝ። እርሱ ፀሎት ሲያደርግልኝ እኔ ማጓራትና መጮህ ጀመርኩ። በርካታ አጋንንት ወጡልኝ። ያኔ ብርሃን ተገለጸልኝ። ሕይወቴ ፈውስ አገኘችና ጌታ ደረሰልኝ።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይግባው። ዛሬ ከራሴ አልፌ ወግ ደርሶኝ ለሌሎች ፀሎት አደርጋለሁ። ምንም እንኳን ዛሬ ፕሮቴስታንት ብሆንም የምሠራበትን የሙስሊሞች ተቋም (ጥናቱ በተደረገበት ወቅት) መልቀቅ አልፈለግኩም። ምክንያቱም ሌሎች ሙስሊሞችን ‹‹ወደ ክርስቶስ ማምጣት›› እፈልጋለሁና። አሁንም ለብዙ የመሥሪያ ቤቴ ባልደረቦች መጽሐፍ ቅዱስ ሰጥቻቸዋለሁ። ጌታን ያገኘሁበትንም ምስጢር በምስክርነት አውጃለሁ። ታሪኬን ያደመጡም ብዙዎች ጌታን ተቀብለዋል። ‹ኢየሱስ ጌታ ነው› ብለዋል።››

ይህ ከላይ የተመለከተው ታሪክ ‹‹ተረት›› የሚመስላቸው በርካታ ሙስሊሞች ይኖራሉ። ግን ተረት አይደለም እውነት እንጂ። አብደላ ብቸኛው የከፈረ ሙስሊም አይደለም። በርካታ ቁጥር ካላቸው የቀድሞ ሙስሊሞች አንዱ ነው። አብደላ ቃለ መጠይቁን በሰጠበት ጥናቱ ውስጥ የተካተቱ 252 ሙስሊሞች ተመሳሳይ ታሪክ ለጥናት አቅርበው ነግረውታል።

በላይ ጉታ የተባሉ ግለሰብ ባዘጋጁት "Muslims Evangelism in Ethiopia" በሚለው የጥናት ወረቀት ውስጥ ከአብደላ የባሰና የከፋ ታሪክ ያላቸው የቀድሞ ሙስሊሞች ታሪክ ተካቷል። ተመሳሳይ ታሪኮችንም በየቦታው ማድመጥ አስቸጋሪ እንዳልሆነ ብዙዎች ይናገራሉ። በገንዘብ አቅምም ሆነ በሰበካ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣው የወንጌላውያን (Evangelists) እንቅስቃሴ የሀይማኖተኞቹን ቀጥር በ‹‹አስፈሪ›› ፍጥነት ለመጨመር ከሞላ ጎደል እንደተሳካለት መረጃ ሰጪ ድረ-ገፃቸው ይገልጻሉ። ከነዚህ ድረ-ገፆች መካከል አንዱ እንዳስቀመጠውም በሀገራችን የፕሮቴስታንት አማንያን ቁጥር በ 1960 ከነበረበት 0.8 በመቶ (200,000 ሺህ ሰው) በ 2007 ወደ 18 በመቶ አድጓል።

እዚህ ቁጥር ላይ ለመድረስ እንግዲህ ምን ያህል እንቅስቃሴ እንዳደረጉ ለመረዳት አያዳግትም። እንቅስቃሴያቸውም ሁለገብ ነው ሊባል የሚችል ነው። ሥልጠናዎችን፣ ስፖርታዊ ሰበካዎችን፣ የፊልም ማሳያ ፕሮጀክቶችን ሁሉ ያቅፋል። በ 2000 የተጀመረው ‹‹የአፍሪካ ቀንድ የቤተክርስቲያን ተከላ ፕሮጀክት›› እንደገለጸው ከሆነ እስከ 2010 ድረስ ብቻ በአፍሪካ ቀንድ 10 ሺህ አብያተ ክርስቲያናት ለመገንባት አቅዷል። ከዚህ ወስጥ ደግሞ 65 በመቶው ሊገነባ የታሰበው በኢትዮያና ኬንያ ነው። ይህ ፕሮጀክት በገጠር ወንጌልን ለሚሰብኩ ሰራተኞች በወር 85 ዶላር (ከ1000 ብር በላይ) ከመክፈል በተጨማሪ 135 የሙሉ ሰዓት ሚሽነሪዎችን በኢትዮጵያ አሰማርቷል። ‹‹ውጤቱ በጭራሽ ቀላል እንዳይመስለን›› ይላሉ በዘርፉ ጥናት ሲያደርጉ የቆዩት አቶ ፈይሰል። (ስማቸው ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ተቀይሯል) ‹‹ይህ ፕሮጀክት ባለፉት አምስት ዓመታት 100 ሺህ ሰዎችን ጴንጤ አድርጓል። በድረ-ገፁ እንዳነበብኩት ደግሞ በ 2005 እና 2006 ይህ ፕሮጀክት 65 በመቶውን ድጋፍ ከግለሰቦች፣ 30 በመቶውን ከውጭ ሀገር፣ 5 በመቶውን ደግሞ ከድጋፍ ሰጪ ፈንዶች ነው ያገኘው›› ይላሉ ቁጭት በሚታይበት ፊት።

የተልዕኮ ትምህርቶችም የተለመዱ የሰበካ መንገዶች እንደሆኑ ብዙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ያህል ‹‹ለኢትዮጵያውያን ወንጌልን ማድረስ›› በሚል መሪ ቃል ሥራውን የሚሰራውና በካሊፎርኒያ የሚገኘው ‹‹የዉድዋርድ ፓርክ የኢየሱስ ቤተክርስቲያን›› ለሙስሊም አካባቢዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት የተልዕኮ ትምህርቶችን ሲሰጥ መቆየቱን ገልጿል። ይህ የተልዕኮ ፕሮጀክት በዋነኝነት የአላባ ሙስሊሞችን ለማክፈር ያለመ መሆኑንም እ.ኤ.አ በሚያዝያ 25/2009 ባወጣው ዘገባ አስፍሮታል።

መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎሙም ቢሆን ቀላል የማይባል ሥራ ተሠርቷል ልንል እንችላለን። አዜ ኃይለሥላሴ ካስተረጎሙት የቅዱስ ቁርአን ትርጉም በኋላ በተብራራ መልኩ ቁርአን የተተረጎመው በቅርብ ዓመታት በነጃሺ አሳታሚ አማካኝነት መሆኑን የሚያውቅ ሰው በተለይ በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል የተመዘገበውን ‹‹ስኬት›› በቀላሉ ማየት ይቻለዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ከአማርኛ በተጨማሪ በኦሮምኛና ጉራጊኛ የተተረጎመ ሲሆን ኦሮምኛው ደግሞ የታተመው ከመቶ ዓመታት በፊት ነበር። ይህ ደግሞ ቁርአን ወደአማርኛ ከመተርጎሙ ከስልሳ ዓመታት በፊት እንደነበር ባለሙያው ያስታውሳሉ።

ፊልምን እንደ ዳዕዋ

ፊልም የራስን ባህልና አመለካከት በሰዎች ውስጥ በቀላሉ ለማስረጽ የሚቻልበት መሣሪያ ቢሆንም ለሃይማኖት አላማ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል አልታየም። ወንጌላውያን ግን ይህንን ከሞላ ጎደል ለመቀየር እንደቻሉ ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ›› ሪፖርተር የተመለከታቸው ድረ-ገጾች ያሳያሉ። ለጴንጤዎች ፊልም በከፍተኛ ደረጃ ለሰበካ ከሚውሉ መንገዶች አንዱና ዋነኛው ነው። ወንጌላውያን ትኩረት ሰጥተው በሚንቀሳቀሱበት ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የኢየሱስ ፊልም በየሀገሬው ቋንቋ ተተርጉሞ 3361 ጊዜ ያህል ለእይታ የበቃ ሲሆን 3 ሚሊየን 229 ሺህ 967

ሰዎች አይተውታል። በውጤቱም በክልሉ 42 አብያተ ክርስቲያናት ተገንብተው ‹‹የአማኞች›› ቁጥር በእጥፍ መጨመሩን ድረ-ገፃቸው ይገልጻል። በ 1991 ለመሰበክ ጅማ ወደሚገኘው የፊልም ማሳያ ፕሮጀክት ቢሮ ለመግባት እድል ያገኘውና ስሙን ለመጥቀስ ያልፈለገው ወጣት መሰል ገጠመኙን የሚናገረው በስሜት ነው። ‹‹ይገርማል!›› በሚል ጀመረና ያስገረመውን ነገር ለንግግሩ ድጋፍ በሚሰጠው ፊቱ እያጀበ ነገረን። ‹‹ግድግዳ ላይ ተለጥፎ ያየሁት ሰንጠረዥ ለአምስት ዓመታት ያህል በጅማና አካባቢዋ የኢየሱስን ፊልም ለሕፃናት ለማሳየትና ለተያያዥ እንቅስቃሴዎች 42 ሚሊዮን ብር እንደተመደበ ይገልጻል።›› የዚህን ወጣት ግርምት ብዙዎች ይጋሩታል። ጉዳዩን አስመልክተን ጥያቄ ያቀረብንለት የቀድሞ ወንጌላዊ ታምራት (ስሙ ተቀይሯል) ‹‹ሌላም አለላችሁ› ነበር ያለን። ‹‹ይህንኑ የኢየሱስ ፊልም በመላው ኢትዮጵያ በተለያዩ ቋንቋዎች ለማሳየት 460 ሚሊዮን ዶላር መመደቡ ለእኛ

ለሙስሊሞች ታላቅ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ይህ ገንዘብ ለኢስላማዊ ዳዕዋ ውሎ ቢሆን ምን እንደሚፈጥር አስቡት፡፡››

እንግዲህ ይህ የኢየሱስ ፊልም የሚታየው ሙስሊሞች በሚበዙበት ክልል ሲሆን ደግሞ ተጨማሪ ማሻሻያዎች ይደረጉበታል፡፡ ለምሳሌ በአፋርና በሶማሌ ክልል የሚሠራጨው የኢየሱስ ፊልም የያዛቸው ስሞች የሙስሊም ናቸው፡፡ በፊልሙ ውስጥ ኢየሱስ ዒሣ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ያህያ፣ ማርያም መርየም እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሙስሊሞች ዘንድ የእኔነት ስሜት እንዲፈጠር ደርጋል፡፡ ይህ ምናልባትም ፊልሙ ክርስቲያናዊ ታሪክ መሆኑን ሊያስረሳ የሚዳዳ ተንኮል እንደሆነም አቶ ፈይሰል ይገልጻሉ፡፡

የትምህርት ደረጃቸው	ሁለተኛ ደረጃ 58%	ከሁለተኛ ደረጃ በላይ 12%	ያልተማሩ 18%	አንደኛ ደረጃ 12%
ፆታ	ወንድ 75%	ሴት 25%	-	-
ብሔር	ኦሮሞ 52.4%	አማራ 19.8%	ጉራጌ 18.7%	መናገር ያልፈለጉ 6%
የገቡበት ቤተ ክርስቲያን	ሙሉ ወንጌል 44%	መሠረተ ክርስቶስ 25%	መካነ ኢየሱስ 11.5%	ህይወት ብርሀን 7.1%
ጥሪ ያደረገላቸው	የብሔራቸው ክርስቲያን ሰራተኛ 66.3 %	ከብሔራቸው ውጭ ያለ ሰው 26.3%	ቤተሰባቸው 25.8%	ጓደኛ 55.2%
እንዲሰልሙ አስተዋፅኦ ያደረገ	ስነ ፅሁፍ 38.9%	ሬዲዮ 16.7%	ቲቪ/ቪዲዮ 1.2%	የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት 49.2%
ዳዕዋ የተደረገለት	በግለሰብ ምስክርነት 78.6%	በትልቅ የወንጌል ኮንፈረንስ 5.2%	በክርክር/ውይይት 2.4%	በካሴት 16.3%
ሌላ ተፅዕኖ ያሳደረበት	ኢየሱስን በህልም አየሁ 20.6%	-	-	-
ሌላ ምክንያት	ዱዓዬ ተቀባይነት አገኘ 56.7%	ተዓምር 60.7%	በሙስሊሞች ተግባር መጥፎነት 28.6%	-

ሁሉም ሰው የሚወደው ስፖርት ይኖረዋል፡ ፡ ግማሹ እግር ኳስ፣ ግማሹ ቅርጫት ኳስ፣ ግማሹ ካራቴ ይወዳል፡፡ በመሆኑም በሚወዱት ስፖርት ዳቦ ሥር ሳንዱች ተደርጎ የሚመጣ ሰበካ ውጤታማ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በተለይ ደግሞ እግር ኳስ ብዙዎችን እንቅልፍ አሳጥቶ በየዲሽ ቤቱ የሚያሳድር ጨዋታ

እንደመሆኑ እርሱን ታክኮ የሚመጣው ዳዕዋ ተዕእኖው ቀላል አይሆንም፡፡ ይህን ጠንቅቀው የሚረዱት ወንጌላውያን ዘዴውን በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ ‹‹Sport Friends Ministry in Ethiopia›› አዘጋጅቶ ያወጣው ዳሰሳ እንደሚያትተው ከሆነ ባለፉት 5 ዓመታት ብቻ ከ 4500 በላይ ለሚሆኑ ስፖርተኞች ከ 3-5 ቀናት የሚቆይ ወንጌላዊ ሥልጠና ተሰጥቷል፡ ፡ አራተኛ ደረጃ ሥልጠና ደግሞ ለ55 ሰዎች የተሰጠ ሲሆን 5 ሳምንታት ፈጅቷል፡፡ በዘርፉ ጥናት ሲያደርጉ የቆዩት አቶ ፈይሰል ያጠናቀሩትን መረጃ መሠረት በማድረግ እንደገለጹልን ስፖርትን ታክኮ የመስበኩ ሥራ ላይ እስካሁን 1200 አብያተ ክርስቲያናትና 30 ሺህ ወጣቶች ተካፍለውበታል፡፡ ‹‹በዚህ ስፖርታዊ ፕሮጀክት አማካኝነት ሙስሊሙ በሚበዛበት አካባቢ ብቻ ከ100 በላይ አብያተ ክርስቲያናት የተገነቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 80 ያህሉ በአርሲ ናቸው፡፡ ታዲያ በአርሲ ብቻ በአምስት ዓመታት ውስጥ 15 ሺህ ሰው አክፍረናል ብለው መግለጻቸው ምን ይገርማል?›› ብሎ በመጠየቅ የአቅማቸውን ብርታት ያወሳል፡፡

የሰበካ ስልቶች

ወንጌላውያን ሙስሊሞችን በወንጌል ጎርፍ ለማጥለቅለቅ የነደፏቸው ስልቶች እጅግ በርካታ መሆናቸውን በተደጋጋሚ የሚያሳትሟቸው የህትመት ውጤቶች ይገልጻሉ፡፡ ከመሰል ስልቶቻቸው አንዱ ደግሞ ከእስልምና ወደ ክርስትና የገቡ ሰዎችን ሂደት በማጥናት ምን ሊቀይራቸው እንደቻለ ማወቅ፣ ያወቁትንም ለሰበካ ስልትነት ማዋል ነው፡፡ (በዚህ ላይ ብቻ በመመስረት በ 252 ሰዎች አከፋፈር ላይ የተደረገውን ጥናት ከነሠንጠረዡ እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡) ይህ በተለይ ‹‹የእስልምና ድክመቶች ናቸው›› ብለው በሚያስቧቸው ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመስበክ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡፡ በእስልምና ላይ ብኽርታ ለመንዛትና የተሳሳተ እምነት መሆኑን ለማሳየት የተከተቡት በርካታ መጽሐፍቶቻቸው በዚህ ስልት የተቃኙ ናቸው

የሙስሊሙን መተማመን መስለብ!
በዘርፉ ብዙ ጥናት ካደረጉ በኋላ ‹‹የእግዚያብሄርን ፍቅር ለሙስሊሞች ማካፈል›› የሚለውን መጽሐፍ የጻፉት ቢል ዴኔት የሙስሊሞች ድክመት በማለት በዋነኛት የሚጠቅሱት ‹‹መንፈሳዊ ጉድለትን›› ነው፡፡ እንደቢል ዴኔት አስተሳሰብ ‹‹የሙስሊሞችን አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጎቶች በዋና መነሻነት መጠቀም ውጤታማ መንገድ ነው፡፡››
ለዚህም ነው እንግዲህ ኢየሱስ ለሙስሊሞች ሊያሟላ ስለሚችለው ‹‹ፍቅርና መረጋጋት›› በተደጋጋሚ ከወንጌላውያን የሚሰበክልን፡፡ ‹‹ኢየሱስ ይወድሃል፣ ያፈቅርሃል፤ ውስጣዊ ሰላምን ይሰጥሀል›› የተለመዱ የሰበካ ቃላት ከመሆናቸውም ሌላ ለጆሮም እስኪሰለቹ ተደጋግመዋል፡፡ ይህ ታዲያ ከሙስሊሞች ጋር ሊደረግ የሚችለውን ሀይማኖታዊ ክርክር በተወሰነ መጠን እንደሚያስቀረው ይታመናል፡፡
አሁን አሁን ከተሜዎቹ ሙስሊሞች ስለሀይማኖታቸው ያገኙት የተወሰነ እውቀትና ንቃት ከሚሸነሯዎች ጋር በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉ በር መክፈቱ አንባቢዎቻችን የሚረዱት እውነታ ነው፡፡ በነዚህ ውይይቶች ደግሞ ሁልጊዜም ሙስሊሞች የበላይነቱን ይዘው በመቆየት ተደጋጋሚ ድሎችን ሲያስመዘግቡ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም ፕሮቴስታንት ሰባኪዎች ሽንፈትን ለማስወገድ ውይይቶችን ማስወገድን እንደአማራጭ ይወስዱታል፡፡ ከክርስቲያኖች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረጉ ከስሙ ጎላ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ›› የሚል የተለምዶ ቅጽል ስም የተሰጠው አብዲ ሁሴንም ይህንን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ ይጋራል፡፡ ‹‹ብዙውን ጊዜ ለመጀመሪያው ውይይት በሙስሊሞች ጋባኝነት የሚገኙት እውቀት የለውም ብለው ሲያስቡ ነው፡፡ ስለመጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር የሚያውቅ ሰው ሊከራከራቸው እንደመጣ ሲያውቁ ግን በሁለተኛውና በሦስተኛው ቀጠሮ ይቀራሉ›› ሲል ይገልጸዋል፡፡
የዚህ ሽሽትና አለመጋፈጥ ምንጭ ከሙስሊም ተወያዮች በክርስትና ላይ የሚወረወሩት ጥያቄዎች

ግዘፈትና አደናጋሪነት ነው ልንል እንችላለን፡፡ ለክርስትና እንደ አዕማድ የሚቆጠሩት ሥላሴን የመሳሰሉ ፅንሰ ሀሳቦች እንኳን ለውጭ ሰውና

ለክርስቲያኖችም ግልፅ አይደሉም፡፡ በመሰል አጀንዳዎች ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር እንዳይወያዩ የተለያዩ ጫንጤ ፀሐፍትና ሰባክያን አጽንኦት ሰጥተው የሚያስጠነቅቁትም ከዚሁ አኳያ ነው፡፡ ‹‹የሥላሴ ፅንሰ ሀሳብ በሙስሊሞች ዘወትር የሚነሳ ተቃውሞ ሲሆን አጥጋቢ ማብራሪያ ማቅረብ ከቶውንም አይቻልም፡፡ ...ዲዳትን ከመሳሰሉ ሙስሊሞች ጋር ግልፅ ክርክር
እንዳይከፍቱ ክርስቲያኖችን በጥብቅ እመክራለሁ›› በማለት ቢል ደኤትም ቢሆኑ እውነታውን ለማመን ተገደዋል፡፡ እንደነዚህ ጽሑፎች ሃሳብ አንድ ‹‹የኢየሱስን ፍቅር ለሙስሊሞች ለማካፈል የፈለገ (ለማክፈር የፈለገ)›› ክርስቲያን የፈጠጠ ጥያቄ ሲመጣበት ‹‹እኔ እውቀት የለኝም›› በሚል መተናነስ መጽሐፍ ቅዱስን እራሳቸው እንዲያነቡት ይጋብዛል፡፡ ሰበካ በቀላሉ ማለት ነው! ከሚሲዮናውያን ብዙ የማጥመጃ መረቦች አንዱ እስልምናና የሴቶች መብትን ይመለከታል፡ ዓለም ሲቀባበለውና ሲነጋገርበት በክፍለ ዘመናችን ረጅም እድሜ ያስቆጠረው የዘመኑ ቀመር ‹‹እስልምና ሴቶችን ይጨቁናል›› የሚለው ከእውነታ የራቀመፈክር መሆኑን ዶ/ር ዛኪር ‹‹Most Common Questions asked by Non Muslims›› በሚለው መፅሀፋቸው ይገልፃሉ፡፡ የሴቶች መብት የእስልምና ጥላሸት ቀቢዎች ሁልጊዜም የማይረሱት ነጥብ ነው፡፡ከዚሁ የማጠልሻ ማዕድ የመጀመሪያ ተቋዳሽ የሆኑት ሚሲዮናውያንም ሙስሊሞችን ለማጥመቅ እንደዋነኛ ግብዓት እንደሚጠቀሙበት ዶ/ሩ አክለው ይገልጻሉ፡፡በተደጋጋሚ በሚያወጧቸው ጽሑፎች ሴት በእስልምና ቦታ እንደሌላት፣ ክርስትናን ብትቀበል ግን የኢየሱስ ፍቅር ‹‹እንደሚያለመልማት›› በመስበክየሙስሊም ሴቶችን ልብ ለማሸፈት ይጥራሉ፡፡ የሴቶችን ኢስላማዊ መብት ለማሳወቅ ደግሞ በሙስሊሞችበኩል የተደረገው ጥረት ውሱን መሆኑ ስልታቸውን ከ‹‹ስኬት›› ደጃፍ ለማድረስ አስተዋፅኦ ማድረጉን አስተያየት ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ የኮሚሽን ሥራ ባለሙያው ኢብራሂም ሙነወር ከዚህ የተለየ ሀሳብ የለውም፡፡ ‹‹ምንም እንኳን ...›› ይላል ኢብራሂም በስሜት በተዋጠ ድምፅ፡፡ ‹‹ምንም እንኳን እየተደረገያለው ጥረት ጥሩ ጅማሬ ቢሆንም በጣም ይቀረናል፡፡ ብዙ መበረታታትም ይጠበቅብናል፡፡››

‹‹አስማት›› እና ‹‹ፈውስ››

ከላይ በተጠቀሱት ሀሳቦች እንደተብራራው ጠንካራ የሙስሊም ጥያቄዎችን ለመሸሸና የተለየ ዓይነት ስልትን ለመከተል የሚያስችሉ በርካታ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህ አንዱ ደግሞ ‹‹አስማት›› ነው፡፡ ብዙ ምስኪን ወንድምና እህቶች በዚህ መልኩ ‹‹ሲህር›› (ድግምት) እየተደረገባቸው ቀልጠው እንደቀሩ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ በቅድስት ማርያም ኮሌጅ የአካውንቲንግ ተማሪ የሆነችው ኢክራም አደም የችግሩን መባባስ በምስክርነት ትገልጻለች፡፡ ‹‹በፕሮቴስታንቶች ድግምት ተደርጎባቸው ያለፍላጎታቸው ቸርች የሚመላለሱ፣ ጅልባብና ኒቃባቸውን ያወለቁ ሴቶችን አውቃለሁ ትልና ከእኒህ ሴቶች አንዷ ‹‹እኔን ያየሽ ተቀጪ›› በሚል ያስተማረችበት ትምህርት ላይ መካፈሏን ትገልጻለች፡፡ ከዚህ ባስ ያሉ ሁኔታዎችም ሊያጋጥሙ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ሙስሊሞች ‹‹አጋንንት መጥራት›› ፕሮቴስታንቶች ‹‹መንፈስ መጥራት›› ይሉታል፡፡ አቶ ፊይሰል ያደረጉትን ጥናት ምርኩዝ አድርገው እንደነገሩንም ‹‹የፈውስ ፕሮግራም አለ›› ይባልና መንፈሱን ወደ ሙስሊሙ ያስተላልፋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሰውዬው በራሱ ፍላጎት የሚመራ መሆኑ ቀርቶ አጋንንት ያዘዘውን ይፈጽማል፤ ቸርች ይሄዳል፤ ያጓራል፣ ይወድቃል፡፡ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ገባበት›› ተብሎ ‹‹ሀሌሉያ›› ይባላል፤ ይጨፈራል፡፡ ይህን መሰል ፕሮግራሞች በተለያዩ ቸርቾች የሚካሄዱት በአብዛኛው እሁድ እሁድ እንደሆነ በስተማው የሚለጠፉት ፖስተሮች በደማቁ ይመሰክራሉ፡፡

ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን የማጥመቅ ጥረታቸውን በተለያዩ መንገዶች ከመፈጸማቸው የተነሳ አንዳንዱ እጅግ አስገራሚ ነገሮችን የሚያደርጉበት ጊዜ ያጋጥማል። በገጠርና በከተማ የሚገኙ የሕፃናት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ብዙ ሰበካ ይፈጸማል። ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ›› ያነጋገረቻቸው ሰዎች እንደሰጡት መረጃ ‹‹ኢየሱስ›› እና ‹‹ሙሐመድ›› የሚባሉ ከረሜላዎች ይመረቱና ስም ይጻፍባቸዋል። ከረሜላዎቹ ሲታዩ አንድ ቢመስሉም ጣዕማቸው ግን ለየቅል ነው። ኢየሱስ ከረሜላ ጣፋጭ፣ ሙሐመድ ከረሜላ ደግሞ መራራ! መራራውን ‹‹መሐመድ›› ከረሜላ የቀመሱ ሕፃናት ሊደግሙት አይፈልጉም፤ ይህን ስም ለያዙ ሰዎችም ቀስ በቀስ ጥላቻ እያዳበሩ እንደሚሄዱ ይታመናል። ይህን ድርጊት ብዙሀን ሙስሊሞች ‹‹ተራ ሕፃናትን የማታለያ ወንጀል›› ሲሉ ቢገልጹትም ለሚስዮናውያን ግን ኢየሱስን አጣፍጦ ለሕፃናት የማቅረብ ሂደት ነው።

በዚህ መሰሉ የከረሜላ ማጥመጃ ለማይሸወዱ ተለቅ ያሉ ሙስሊሞች ደግሞ ለየት ያለ ዘዴ ተዘጋጅቷል። በእምነታቸው ደከም ያሉ ሙስሊሞች ይፈለጉና እስልምና ‹‹ውጤታማ›› እንዳላደረጋቸው ይነገራቸዋል። አቶ ፈይሰል እንዲህ ይገልጹታል። ‹‹‹እስላም ነህ፣ ሁልጊዜ ዱዓ ታደርጋለህ፣ ግን ውጤቱ የታለ? አላህ መቸ ፀሎትህን ሰማህና?› እያሉ የሰውየውን ሆድ ያባቡታል። ኢየሱስን ቢጠይቅ ፀሎቱ ወዲያው ተቀባይ እንደሚሆን ምሳሌዎችን በመንገር ያሰለቹታል። የተከታዮቻቸውን ቁሳዊ ሀብት እያሳዩ ያስጎመጁታል። ይሄኔ የሰውዬው እምነት መሸርሸር ይጀምራል። ደግሞ ጉዳቱ ይህ ሁሉ ጥሪ የሚደረገው በየሀገሬው ቋንቋ መሆኑ ነው።››

<u>የቀድሞ ወንጌላውያንና ፖስተሮች ተሞክሮ</u>

ኢስላም በዓለም ላይ ካሉ ሀይማኖቶች ሁሉ በፍጥነት እየተስፋፋ ያለ ሀይማኖት ነው። በ 1900 የነበሩት 150 ሚሊዮን ተከታዮች በአሁኑ ሰዓት 1.1 ቢሊዮን ደርሰዋልል። ከቅኝ አገዛዝ ዘመን በኋላ ሙስሊሞች ፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ዕድገት አሳይተዋል። ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ ሀብቶቻቸው የተነሳ የሙስሊሞች ኢኮኖሚ ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል። በነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ ወንጌልን ለሙስሊሞች ማድረስ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ግዴታ እንደሆነ በጌርሀርድ ኔልስ የተዘጋጀው ‹‹ወንጌልን ለሙስሊሞች››የተሰኘው መፅሀፍ አፅንኦት ሰጥቶ ያትታል። ይህንን ግዴታ ለመወጣትም በጥናት የተደገፈ ጠንካራ የማክፈሪያ ስልት አስፈላጊ በመሆኑ ለሙስሊሞች ብቻ የተለያዩ መርሀ ግብሮች ተነድፈው ወንጌላውያንን ማሰልጠኛ ማእከሎች ይቋቋማሉ።

‹‹እነዚህ ተቋማት ‹ሙስሊም ኢቫንጀሊዝም› የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው ለወንጌላውያን ሙስሊሞችን ማጥመድ የሚችሉበትን መንገድ ያስተምራሉ። ወንጌላውያኑ ስልጠናውን ሲጨርሱ

በድንበር የለሽ ሚሽነሪ ማዕረግ ወደመጡበት ክልል ይላካሉ›› ይላሉ በሙስሊም ኢቫንጀሊዝም ፕሮግራም የሰለጠኑት የቀድሞ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ወንጌላዊ። ሙስሊሞችን ለማጥመድ በርካታ ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ የሚገልፁት ቀድሞው ፓስተር ደረጀ ወደሙስሊሞች አካባቢ ሲሄዱ ጀለቢያ ለብሰው፣ ስማቸውን ቀይረውና ሙስሊሞችን ተመሳስለው እንደነበር ያስረዳሉ።

ይህን ነጥብ በ 1988 ‹‹የምስራቹን ቃል ማድረስ›› በሚል የታተመው የፕሮቴስታንት መምህራን መመሪያ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡ ‹‹ምግባቸውን መመገብና እንደነርሱ መኖር፣ እንደእስላም መልበስ፣ ለእስላም መሪዎች ሰላምታ ማቅረብና እስላሞችን መጎብኘት ወንጌልን ለእስላሞች ለማድረስ ሁነኛ መንገድ ነው።›› ኢስላምን ከተቀበሉ ገና አንድ አመት እንኳ በቅጡ ያልሞላቸው የቀድሞው ወንጌላዊ ታምራት ሙስሊሞችን ለማጥመድ ሌላው መንገድ ሙስሊሞች በሚገባቸው በራሳቸው ቋንቋና ከባህላቸው ጋር በሚሄድ መልኩ ወንጌልን ማቅረብ እንደሆነ ይገልፃሉ። ለዚህም አባባላቸው የኢየሱስ ፊልምን ፕሮጀክት እንደማስረጃ ያቀርባሉ። ኢየሱስ ፊልም ሲሰራ ሙስሊሞች በሚበዙባቸው ብሄሮች ቋንቋና የሙስሊሞችን ባህል ባጣጣመ መልኩ እንዲሰራ በቅድሚያ ከፍተኛ ጥናት ተደርጓል። በዚህም ጥናት መሰረት በአፋርኛ፣ በስልጢኛ፣ በአላብኛና በመሳሰሉት በርካታ ሙስሊሞች በሚናገሯቸው ቋንቋዎች ለባህላቸው ቅርብ በሆነ መልኩ ፊልሙ ተተርጉሞ ቀርቧል።

ፊልሞቹን ልብ ብሎ ለተመለከተ ሰውም በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችሉ ተመሳሳይ ነገሮችን ያስተውላል። በፊልሙ ውስጥ ኢየሱስን የሚወክለው ገፀ-ባህሪ የሚጠራው ሙስሊሞች በሚያውቁት ‹‹ዒሳ›› በሚለው

ስም ነው፡፡ የአምላክ ስምም ‹‹እግዚአብሔር›› ወይም ‹‹ጎድ›› አይደለም - አላህ እንጂ፡፡ በዚህም ሙስሊሞች የእኔነት ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ የሚፈለገው መልዕክት በቀላሉ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

ሙስሊም የሀይማኖት መሪዎችንና ባለስልጣናትን፣ እንዲሁም ተሰሚነት ያላቸውን የጎሳ መሪዎች በጥቅማ ጥቅሞች መደለል ሌላው መንገድ እንደሆነ ከ 26 አመታት በላይ በፓስተርነት የሰሩና በ 1998 ኢስላምን የተቀበሉ አንድ ምሑር ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ማረጋገጫም 7000 ኪሎ ሜትሮችን ለመንገዝ አቅዶ ከጀርመን የተነሳውን የአሜን ፕሮጀክት ይጠቅሳሉ፡፡ ይህ ፕሮጀክት በየደረሰባቸው አገሮች ለሚገኙ የሀይማኖት መሪዎች ከፍተኛ ስጦታዎችን በመስጠት ተልዕኮውን በህቡዕ ለማሳካት ጥረት አድርጓል፡፡ እኚሁ ምሁር እርሳቸው ፓስተር በነበሩበት ወቅት ከውጪ ዜጎች ጋር በመሆን ወደ አልከስዬ ሄደው እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ‹‹የጎሳና የሀይማኖት መሪዎችን ጴንጤ እንዲሆኑ አትሰብካቸውም፡፡ ይልቁንም የስጦታ ጎርፍ እንዲያጥለቀልቃቸው በማድረግ ተሰሚነታቸውን

ተ.ቁ	ብሔረሰብ	የከፈረ ሰው ብዛት	በመቶኛ
1	የሜጫ ኦሮሞ	1,118,000	25%
2	የአርሲ ኦሮሞ	50,421	2.1%
3	ሊቢዶ (ማረቆ)	5,100	10%
4	አፋር	1,360	0.1%
5	ኢሮብ	1,176	12%
6	ሀመር በና	1,088	1.7%
7	ሱማሌ	439	0.01%
8	አላባ	336	0.2%
9	ዑዱክ	261	0.9%
10	ቤጊማያ	110	2.5%
11	የቦረና ኦሮሞ	66	0.6%
12	ሱሪ	55	0.22%
13	ሀደሬ	33	0.1%
14	አንፊሎ	17	1.0%
15	ስልጤ	ጥቂት	-
16	የጁ ኦሮሞ	ጥቂት	-

ትጠቀምበታለህ፡፡ ‹እነ እገሌ ጥሩ ሰዎች ናቸው፤ የሚሏችሁን ተቀበሏቸው› ብለው ለህዝቡ እንዲናገሩ ታደርጋቸዋለህ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው እዳው ገብስ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ስላላቸው ህዝቡ የምትለውን ሁሉ ይቀበልሀል›› ይላሉ ከአመታት በፊት የነበራቸውን

ልምድ እያስታወሱ። መስጂዶች ውስጥ ሁካታና አለመረጋጋት እንዲፈጠር ማድረግም ሌላው ዘዴ ነው። የቀድሞው ፓስተር ደረጀ እርሳቸው በሰለጠኑበት ሙስሊም ኢቫንጀሊዝም ተልዕኮ ሙስሊሞችን ተመስሎ ወደመስጂድ መግባትና ክፍፍል ሊፈጥሩ የሚችሉ ርዕሶችን ሆን ብሎ ማንሳት፣ በሶላት ወቅት ውጪ ያለ ሰው ስልክ እንዲደውል ማድረግና ሰጋጆችን ሶላታቸው ላይ እንዳያተኩሩ እንቅፋት መፍጠር ሙስሊሞችን ለማዳከም ከሚገለገሉባቸው መንገዶች አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ። በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ ይላሉ እኒህ የቀድሞ ፓስተር ‹‹ኢማም ሆነው በየመስጊዱ እያሰገዱ የሚገኙ በርካታ ጴንጤዎች መኖራቸው ነው። በፕሮቴስታንት ቀኖና መሰረት እምነት የሚገለፀው በልብ ነው። ስለዚህ አንድ የመስጂድ ኢማም በተመሳሳይ ጊዜ ኢማምም ጴንጤም ሊሆን ይችላል። የዚህ ኢማም ዋና ተግባርም መስጂዱ ውስጥ ክፍፍሎች እንዲፈጠሩ መስራት ነው። ይህ ዘዴ በተለይ በርካታ ሙስሊሞች በሚገኙባቸው በአፋርና በሱማሌ ክልሎች በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል።››

ከነዚህ መበንገዶች በተጨማሪ የእርዳታ ድርጅቶችን መጠቀምን እንደ አንድ ዘዴ ይገለገሉበታል። ‹‹ኮምፓሽን›› በተሰኘው የዕርዳታ ድርጅት ውስጥ ለአምስት አመታት ያገለገለው አቶ ዮሀንስ ‹‹እርዳታ›› የሚለውን ቃል ሊሰማቸው ከማይፈልጋቸው ቃላት ጎራ ይመድበዋል። በድርጅቱ በቆየባቸው አምስት አመታት ሙሉ ድጋፍ የሚደረግላቸው ቤተሰቦች ስንዴ፣ ዘይት ወይም ብርድ ልብስ ብቻ ይዘው ወደቤታቸው አይሄዱም - የፕሮቴስታንት እምነትን ቀኖናዎች ጭምር እንጂ! በእርዳታ ስም የሚደረጉ የሀይማኖት ዘመቻዎች በበርካታ ሀገራት እንደሚተገበሩ ዶ/ር አህመድ ሸፋዓት “Towards Building Muslim Strength” በተሰኘው መጣጥፋቸው ያትታሉ። በሀገራችንም በዕርዳታ ስም ከፍተኛ የማክፈር እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ድርጅቶች መሀል “World Vision” እና “Christian Children Fund” እንደሚገኙበት የቀድሞዎቹ ፓስተሮች ገልፀዋል።

ዋይ ገንዘብ!

ሚሲዮናውያንን ለ‹‹ስኬት›› ያበቁ ድክመቶቻችን በርካታ እንደሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ። እኒህ ድክመቶች ደግሞ ከእነሱ ጥንካሬዎች ጋር ሲደመሩ የሚፈጠረው ተፅእኖ ቀላል እንዳልሆነ ጨምረው ይገልጻሉ። በግል ሥራ ላይ የተሠማራው ዳዒ አህመድ ሙስጠፋ የእንቅስቃሴያቸው ዋነኛ ጥንካሬ አነሳሱ ፖለቲካዊ መሆኑ እንደሆነ የሚገልጸው በፍጹም እርግጠኝነት ነው። ‹‹ፕሮቴስታንቲዝም የኢምፔሪያሊዝሙ ዓለም (የመሪዎች) ሀይማኖት በመሆኑና የተጀመረውም የኸሊፋው ሥርዓት በወደቀበት፣ ሙስሊሞች በተዳከሙበት ሰዓት በመሆኑ ተሳክቶለታል›› ይልና ወደ ሀገራችን ስንመጣ ግን የስኬታቸው ቁልፍ ‹‹የሙስሊሞች አንድነት ማጣት›› መሆኑን በቁጭት ይገልጻል።

ስሙን መግለጽ ያልፈለገ አንድ ሙስሊም ምሁር ደግሞ የተለየ ሀሳብ ያነሳል። ‹‹ዋናው ችግር›› ይላል ምሁሩ ‹‹ዋናው ችግር የኛ የእርዳታ ድርጅቶች በመንግሥት ዘንድ በጥርጣሬ መታየታቸው ነው። የእነሱ ድርጅቶች በነፃነት እየተንቀሳቀሱ ሺዎችን ሲያከፍሩ የእኛዎቹ ግን በሽብርተኝነት ይጠረጠራሉ፤ ፍቃድ ሲጠይቁም የጎሪጥ ነው የሚታዩት›› ይላል። ይህ ችግር ሥር የሰደደ መሆኑን ሌሎች አስተያየት ሰጪዎችም ይጋሩታል።

ከ50 በላይ የአማርኛ ኢስላማዊ መጽሐፍትን የተረጎመውና ያዘጋጀው ኡስታዝ ሐሰን ታጁ ኢስላምንም ጃሂሊያውንም (ከኢስላም ውጭ ያለውን ሥርአት) ካለማወቅ ቀጥሎ በሁለተኛነት የሚያቀርበው ድክመት ከላይኛው ብዙም አይለይም - ዳዒ ተቋም አለመኖር! ‹‹ወደኢስላም የሚጣሩ ግለሰቦች እንጂ ዳዒ ተቋም (ዩኒቨርስቲ) የለንም። አናሳ በሆነው የግለሰብ ዳዒዎች ጥረት ደግሞ ሚሲዮናውያንን መቋቋም ከባድ ነው›› ይላል።

የ‹‹ዳዒ ተቋም›› አለመኖር እንቅስቃሴው ጠንካራ ገጽታ እንዳይኖረው ያደርጋል። ምክንያቱ ግልጽ ነው። የግለሰቦች ጥሪ ከግለሰቦች ህልውና ጋር የሚያያዝ በመሆኑ እድሜው ሲያጥር ተቋም ግን የተሻለ እድሜና የተደራጀ ሥራ እንደሚኖረው ይታመናል።

አህመድ መስጠፋ ሌላም እንደ ድክመት የሚቆጥረው ጉዳይ አለ - የገንዘብ ጉዳይ። ‹‹መስሊሞች ለዳዕዋ የምናውለው እዚህ ግባ የሚባል የገንዘብ መጠን የለንም። በተለይ ብዙ ሰዎች አረቦች ከፍተኛ የዳዕዋ ገንዘብ የሚያፈሱ ቢመስላቸውም እውነታው ፍጹም ተቃራኒ ነው›› ባይ ነው።
እውነታውም ከዚህ ብዙ አይርቅም። ሚስዮናውያን ገንዘብ የሚያፈሱት በገፍ ነው። ዘይቱ፣ ዱቄቱ፣ ሕክምናው፣ እርዳታው ማለቂያ የለውም። በተለይ ደግሞ የብዙ ዓለማቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች በጀት የሚውለው ለሰበካ ይሁን ለእርዳታ የማይለይበት ጊዜ አለ። ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉት ምሁር ይህንን ከዋነኞቹ ችግሮች ጎራ ይመድቡታል። እንደምሁሩ አመለካከት ከሆነ የእርዳታውም የሰበካውም ገንዘብ መለየት በማይቻል ሁኔታ ተደበላልቋል። በመሆኑም ‹‹እርዳታ›› በሚል ታጊላ የሚመደበው በጀት ‹‹የወንጌል ሥርጭት ገባር ወንዝ›› ሆኖ ያርፋል። እኒህ በጀቶች አስደንጋጭ ግዝፈት ያላቸው ናቸው።

‹‹ለምሳሌ›› ይላል አህመድ መስጠፋ ‹‹ለምሳሌ CRDA ብቻውን ለአንድ ሚሲዮናዊ ድርጅት 40 ሚለዮን የኢትዮጵያ ብር ረድቷል። ይህ ገንዘብ ለዳዕዋ ቢውል ምን ያህል ሰው ያሰልም እንደነበር ገምቱ›› በስሜት ነበር የገለጸልን። አንድነት ማጣታችንም ዋነኛ ችግር እንደሆነ ብዙዎች በአጽንኦት ይናገራሉ። ሐሰን ታጁም ይህንኑ ይጋራል። ‹‹እኛ መስጂዶቻችን ውስጥ እርስ በርስ በቃላት ስንቆራቆስ ለነሱ ተመቻቸላቸው፤ ሌሎችን ወደ ኢስላም መጥራቱንም እርግፍ አድርገን ተውነው›› የሚል ሀሳብ ነው ያለው።

<u>መንገዱ ወዴት ነው?</u>

የችግሩ ከፍታ እና ጥልቀት ይህን ያህል ግዙፍ ቢሆንም ለእሱም ቢሆን ጥረት ማድረግ ከተቻለ መፍትሄ እንደማይጠፋለት የመስሊሞች ጉዳይ ያነጋገረቻቸው የሀይማኖት አዋቂዎችና የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ይገልጻሉ። አቶ ፈይሰል ችግሩ ከከተሞች ይልቅ በገጠር ከተሞች የሚስተዋል በመሆኑ ጠንከር ያለ የዳዕዋ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ። ‹‹ገጠሩን ረስተነዋል›› በማለት ዝንጉነታችንን ያስታውሱናል። ምሁር ሐሰን ታጁም የአቶ ፈይሰልን ሀሳብ በመንተራስ የገጠር ሀይማኖታዊ ት/ቤቶች (የቂርአት ማእከላት) ለገጠሪቱ ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ ህይወት መጎልበት የሚጫወቱትን አይነተኛ ሚና በማስመር የእነዚህን ቁጥር ማበራከት ከችግራችን አንዱ መውጫ መንገድ እንደሚሆን ያመለክተናል።
የኢትዮጵያ መስሊሞች ከሌላው የዓለም መስሊም በአካልም በሥነ-ልቦናም የተነጠሉና የራቁ እንደሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ። ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ከእስልምና ጋር የተቆራኘችበት ታሪካዊ እውነታ ቢኖርም አሁን ይዜ ሁሉ የመረሳት ያህል እየደበዘዘ መጥቷል። የሀገሪቱ ቀደምት ዜጎች ለእስልምና የሰሩትን ውለታ የዓለም መስሊሞች መመለሻ (መክፈያ) ጊዜ እየጠበቁ እንደሆነ መሐመድ ጠይብ የጻፉት ‹‹ኢትዮጵያ እና እስልምና›› የሚለው መጽሐፍ ያትታል። ወጣቱ ዳዒ አህመድ መስጠፋ ‹‹ይህን እድል ለምን አንጠቀምበትም?›› ሲል ይጠይቃል። ከሌላው ዓለም ጋር የምናደርጋቸው ግንኙነቶችም ሁለት ጥቅሞችን መሠረት ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል። የመጀመሪያው የእውቀት ሽግግርን ይመለከታል። የኢትዮጵያ መስሊሞች ከሌላው ዓለም መስሊሞች ሀይማኖታዊም አካዳሚያዊም እውቀት ያለከልካይ ማግኘት ይችላሉ። እንደ አህመድ ገለፃ ያሉብንን የፋይናንስ ችግሮችም ጥቂት ጥረት ብቻ በማድረግ መቅረፍ ይቻላል። ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት ምሁርም መስሊም የውጭ እርዳታ ድርጅቶች በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ቢፈቀድ ሁኔታውን ሊለውጠው

እንደሚችል ያምናሉ።
ከኢትዮጵያ መስሊሞች ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ አስኳሉ የመሪ እጦት ነው። ከመስጊድ የኮሚቴዎች ስብሰባ እስከ ላይኛው የመጅሊስ ጸ/ቤት ድረስ መስሊሙ በአመራር ቀውስ ይታመሳል። በየጊዜው በመስሊም ተቋማት ውስጥ የሚነሱ የ‹‹ሥልጣን ይገባኛል›› ግጭቶች የመስሊሙን ማህበረሰብ እድገትና ተጠሪነት ወደኋላ ሲጎትቱ ተስተውለዋል። በኢትዮጵያ ትልቁ የሆነው የመስሊሞች ተቋም ከሐጅና ዑምራ የዘለለ ቁምነገር መሥራት አለመቻሉ ቅስማቸውን እንደሰበረው በታላቁ አንዋር መስጊድ ውስጥ አግኝተን ያነጋገርናቸው ምዕመናንም ይገልጻሉ። ሰፊ የሆነው መስሊም ማህበረሰብ ውሃ በማያነሳ ምክንያት ቁጥሩ እየተዘለዘለ ለሚስዮናውያን ገቢር መሆኑ ላብዛኞች አሳዛኝ ክስተት ነው።

‹‹የመጅሊስ ተቋማዊ መሠረት ጠንካራ ቢሆን ችግሩ እዚህ ድረስ ባልደረሰ›› ይላል ሐሰን ታጁ፡፡ ‹‹መጅሊሱ ከሐጅና ዑምራ በዘለለ ጠንካራ ኢስላማዊ ሥራዎችን ለመሥራት መጠናከር አለበት፡፡››
የንጽጽር ሀይማኖት ስራዎችን ዘርፈ ብዙ በሆኑ የህትመት ውጤቶች ማሰራጨትና የሚሠሩበትን ቋንቋ ቁጥር ከፍታ መጨመርም ሌላው እንደ መፍትሄ ተደርጎ የሚወሰድ አማራጭ ነው፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቋንቋዎችን የሚያውቁ ግለሰቦችን በንጽጽር ሀይማኖት ትምህርት አሰልጥኖ በየገጠሩ ማሰራጨት በብዙ መልኩ ሊጠቅም ይችላል፡፡ ሚሽነሪዎች የማህበረሰቡን ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎችን ለሰባኪነት እንደሚጠቀሙ የሚያስታውሱት አቶ ፈይሰል በውጤቱ ብዙ መጠቀም እንደቻሉ ይናገራሉ፡፡ ‹‹ለኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ኦሮምኛ የሚችል የንጽጽር ሃይማኖት መምህር፣ ለጉራጌው ጉራጊኛ፣ ለሲዳማው ሲዳምኛ ቋንቋ ተናጋሪ መምህር ቢዘጋጅ ውጤቱ የት በደረሰ›› ይላሉ፡፡ የንጽጽር ሀይማኖት ትምህርት ለኩፍር ሰለባ ሊሆን የሚችለውን ሙስሊም ጠያቂና ሞጋች የሚያደርግ በመሆኑ ሁሌም ለሚሽነሪዎች ፈተና ይሆናል፡፡ ጥያቄዎቹን ለመመለስና ሙስሊሙን ለመደለል ፈተናው ከባድና አድካሚ ይሆንባቸዋል፡፡ ‹‹ለጥያቄዎቹ መልስ ፍለጋ ይባዝናሉ›› ይላሉ አቶ ፈይሰል፡፡ በከተማው የሚኖሩ የገጠር ተወላጆች በየአካባቢያቸው የተወሰኑ የንጽጽር ሃይማኖት ሥራዎችን ማበራከት ቢችሉ ውጤቱ ሊናቅ የሚችል አይሆንም፡፡ በተለይም በድምፅ ብቻ የተዘጋጁ ሥራዎች አንባቢ ለሌላቸው አካባቢዎች የሚሰጡት ጠቀሜታ የትየለሌ ነው፡፡
አብደላ ዛሬም ሙስሊሞችን ሰብኮ ‹‹ወደ ጌታ ለማምጣት›› ጥረት እያደረገ ነው፡፡ እሱ ‹‹እየተሳካልኝ ነው›› ይላል፡፡

.....እኛስ?